መልእክተ

ኢሰመጉ

ቁጥር 1 ጥር 2014 ዓ/ም

"የመንግስት ባለስልጣኑም ሰራተኛውም ከመንግስት ጋር ንክኪ ያለው ሁሉ ሌብነት ስራ ነው የሚለውን የአቶ መለስ ዜናዊን መመሪያ እየተገበረ ነው"

ወቅቱ ጥር ወር 2008 ዓ.ም ነው። በመላው ኦሮሚያ ለሥርዓቱ አልገዛም የሚለው ህዝባዊ እንቢተኝነት ጎልቶ የወጣበት ነው። ህዝባዊ ተቃውሞ ተፋፍሟል። መንግስት ደግሞ ተቃውሞውን በመሳሪያ ኃይል አቆመዋለሁ ብሎ ስለወሰነ ይገላል፣ ያቆስላል፣ ይደበድባል፣ ያስራል፣ ያፈናቅላል። በዚያው ልክ ህዝቡ ሥርዓቱ አንገፈግፎታል። በመንግስት ህጋዊ እውቅና ሙስናው፣ አድሎው፣ኢ-ፍትሀዊ አሰራር ሰፍኗል። የመንግስት ባለስልጠኑም ሰራተኛውም ከመንግስር ጋር ንክኪ ያለው ሁሉ ሌብነት ስራ ነው የሚለውን የአቶ መለስ ዜናዊን መመሪያ እየተገበረ ነው። በመላው ኦሮሚያ ህዝቡ በሰላማዊ ተቃውሞ መንግስት ደግሞ በመሣሪያው ተፋጧል. . .

3

"በ 6ኛው ሀገራዊ ምርጫና ተግዳሮቶች የወደፊት እርምጃ"

"ዲሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች"

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) "በ 6ኛው ሀገራዊ ምርጫና ተግዳሮቶች የወደፊት እርምጃ" በሚል ርዕስ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ውይይት እያደረገ ነው። የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች፣ ምሁራን፣ ታዋቂ ሰዎች፣ የመገናኛ ብዙኃን አባላት፣ አክቲቪስቶች፣ የማህበረሰብ ተወካዮች በውይይቱ ላይ ታድመዋል።

እስካሁን በተደረጉ ውይይቶች ጥር 12 እና 13 አዲስ አበባ ራዲሰን ብሉ ሆቴል የተከናወነ ሲሆን ጥር 16 እና 17 በሐዋሳ ከተማ ሳውዝ ስታር ሆቴል ተደርጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በባህር ዳር በዩኒስ ሆቴል ጥር 19 እና ጥር 20/2014 ዓ.ም.በፖለቲካ ፓርቲ እና በምሁራን ስብስብ ውይይት ተደርጓል።በተመሳሳይ ሁኔታ በአዳማ ከተማ በሮቢ ሆቴል ከምሁራን እና ከማህበረሰ ተወካዮች በተሰባሰቡ ታዳሚዎች ጥር 23/2014 ዓ.ም. ውይይት መደረጉን ማወቅ ተችሏል።

ከጽ/ቤቱ ባገኘነው መረጃ መሠረት የ2022 እ.ኤ.አ. የበጀት ዘመን በመሠረታዊ የሰብአዊ መብቶች ላይ የሚሰጡት ሥልጠናዎች በሁሉም ቀጠናዎች በቅርቡ መሰጠት እንደሚጀምር ማወቅ ተችሏል።

"የ30 ዓመታት ሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን እየመረመረ ሪፖርት የሚያወጣ ብቸኛ ድርጅት"

/ኢሰመጉ/ ዋና ዳሬክተር
አቶ ዳን ይርጋ ኃይሌ

ኢሰመጉ የተመሠረተው መስከረም 29 ቀን 1984 ዓ.ም.ነው። ኢሰመጉ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው። ዓላማውም በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግ ነው፡. . .

4

ማይካድራ የዘመናችን ኦችዝም?

6

ርዕሰ አንቀጽ

ሀገራዊ ምክክር ፖለቲካዊ ውጥረቶችን ለመፍታት መሠረት የሚሆኑ መፍትሔዎችን ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ኢሰመጉ ያምናል

በሀገራችን በሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካና የሐሳብ መሪዎች እንዲሁም የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሐሳብ ልዩነቶች እና አለመግባባቶች አልፎም ከፍተኛ እልቂትን ያስከተሉ ግጭቶች ተከስተዋል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እና አለመግባባቶችንም ለማርገብ ሰፋፊ ሀገራዊ የህዝብ ምክክሮችን አካታች በሆነ መንገድ በማካሄድ አገራዊ መግባባት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ መንግስት የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን በማጽደቅ፣የኮሚሽነሮች ጥቆማ በማካሄድ እና ሌሎችንም እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህ ሀገራዊ ምክክር አገሪቷ ውስጥ እየተስተዋሉ ያሉ ፖለቲካዊ ውጥረቶችን ለመፍታት መሠረት የሚሆኑ መፍትሔዎችን ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ኢሰመጉ ያምናል።

ይህ ሀገራዊ ምክክር እንዲሁም በመቋቋም ላይ ያለው ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን የያዘውን እና የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ከመንግስት እና ከባለድርሻ አካላት የሚጠበቁ ኃላፊነቶች አሉ። መንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ኮሚሽኑ ሥራውን በሚሰራባቸው ጊዜያት ሁሉ ተጽዕኖ ከማሳደር ታቅበው የኮሚሽኑን በነፃነት የመስራት ሂደት ሊያከብሩ ይገባል። በተጨማሪም ሀገራዊ ምክክሩን የተሳካ ለማድረግ መንግስት እና ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን መወጣት ይገባል። የሚደረጉ ውይይቶች ፖለቲካዊ ውጥረቶችን ለማረገብ፣ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያሉ አለመግባባቶችን በዘላቂነት ለመፍታት እና በአጠቃላይ ሀገራዊ አንድነት እና ሰላምን የመገንባት እሳቤን ይዘው የሚደረጉ ሊሆን ይገባል።

በተለይም በተደጋጋሚ ጊዜ ሲሆን እንዳስተዋልነው የህብረተሰቡ አጀንዳ ሆነው ማህበረሰቡ ሊወያይባቸው የሚፈልጋቸውን ጉዳዮች መድረኩን በሚይዙት አካላት በተለያየ መልኩ ሲጨፈለቁና ወደ መድረክ ቀርበው ሐሳብ ሳይሰጥባቸውና የጋራ መግባባት ላይ ሳይደረስባቸው ቀርተዋል። በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ መሰል መድረኮች ላይ ያለው አመኔታ እንዲቀዛቀዝ ከማድረጉም በላይ እንደዚህ ዓይነት ስብሰባዎች ችግሮችን ለይተው ዘላቂ የሆነ የጋራ መፍትሄ ማመንጫ መሆናቸው ላይ ጥርጣሬን የሚያጭር ሆኗል። በመሆኑም ይህ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን እስከዛሬ የቆየውን የእኔ አውቅልሃለው መንፈስ ወደጎን በመተው ሁሉም ባለድረሻ አካላት ማለትም ህብረተሰቡ፣ በየደረጃው ያሉ የማህበረሰብ ተወካዮች ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበረሰቡ አባላት፣ የእምነት አባቶች እና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት በአግባቡ ባማከለ እና የጉዳዩ ባለቤትነትን መንፈስ በሚፈጥር መልኩ ችግሮቻቸውን በመለየትም ሆነ መፍትሄ በማመንጨት ቀዳሚውን ድርሻ በመያዝ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ ኢሰመጉ ያሳስባል።

አሳታሚ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7

የቤት ቁጥር= 112/37

ስልክ ቁጥር =0118685706

ፖ.ሳ.ቁ =2432

ኢሜል= info@ehrco.org

አዘጋጆች

ብዙአየሁ ወንድሙ

ዳን ይርጋ

ተስፋዬ ገመቹ

ደረጀ መላኩ

አዛሪያ ሰለሞን

አምደኞች

ሊያለም ከበደ

ወንድሙ ኢብሳ

ዳንኤል ተስፋዬ

> በአገሪቱ የተንሰራፋውን ሙስና፣ ሌብነት እና ዝርፊያ ተከትሎ የወረዳው ካቢኔና ባለስልጣናት የድርሻቸውን ሊዘርፉ ወደ ትምህርት ቤቱ ሄዱ። የትምህርት ቤቱን እግር ኳስ ሜዳ ቤት ሊሰሩበት እየመተሩ መከፋፈል ጀመሩ። "የልጆች መጫወቻ ሜዳ ላይ እንዴት ቤት ይሰራበታል?ልጆቹ ምን ላይ እየተጫወቱ ሊያድጉ ነው።እረፍት ሲወጡስ የት ሊያርፉ ነው"ብሎ አንድ መምህር ሲናገር ተማሪዎች ይሰማሉ። ወዲያውኑ ህፃናቶቹ ኳስ መጫወቻ ሜዳችን ኡ! ኡ! ኡ!ሲሉ . . .

የመርማሪው ማስወሻ

"የመንግስት ባለስልጣኑም ሰራተኛውም ከመንግስት ጋር ንክኪ ያለው ሁሉ ሌብነት ስራ ነው የሚለውን የአቶ መለስ ዜናዊን መመሪያ እየተገበረ ነው"

ብዙአየሁ ወንድሙ

እንደ መግቢያ

ወቅቱ ጥር ወር 2008 ዓ.ም ነው። በመላው ኦሮሚያ ለሥርዓቱ አልገዛም የሚለው ህዝባዊ እንቢተኝነት ጎልቶ የወጣበት ነው። ህዝባዊ ተቃውሞ ተፋፍሟል።መንግስት ደግሞ ተቃውሞውን በመሳሪያ ኃይል አቆመዋለሁ ብሎ ስለወሰነ ይገላል፣ ያቆስላል፣ ይደበድባል፣ ያስራል፣ ያፈናቅላል። በዚያው ልክ ህዝቡ ሥርዓቱ አንገፈገፎታል። በመንግስት ህጋዊ እውቅና ሙስናው፣ አድሎው፣ኢ.-ፍትሀዊ አሰራር ሰፍኗል። የመንግስት ባለስልጠኑም ሰራተኛውም ከመንግስር ጋር ንክኪ ያለው ሁሉ ሌብነት ስራ ነው የሚለውን የአቶ መለስ ዜናዊን መመሪያ እየተገበረ ነው። በመላው ኦሮሚያ ህዝቡ በሰላማዊ ተቃውሞ መንግስት ደግሞ በመሣሪያው ተፋጧል።

ቤት በመቀመጥ ተቃውሞውን የጀመረው የጎንደር ህዝብ ወደ አደባባይ ተቃውሞ ቀይሮታል። በኦሮሞ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ግድያ በግልፅ ተቃውመ። <<የሚፈሰው የኦሮሞ ደም ደሜ ነው>> ሲል አጋርነቱን መፈክር ይዞ በመውጣት ገለፀ። የጎንደሮች ሰልፍ ይዘውት የወጡት መፈክር ለመንግስት አስደንጋጫ ሆነ። በወቅቱ የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትር የነበረው አቶ ጌታቸው ረዳን በእጅጉ ስቆጣ። ጋዜጠኞችን ጠርቶ <<እሳትና ጭድ እንዴት አንድ ይሆናል>> ሲል ጠየቀ። በመቀጠልም <<አማራና ኦሮሞ አንድ ሆነ ማለት እኛ የቤት ስራችንን አልሰራንም ማለት ነው>> ሲልም አከለበት። አለቆቹ በድበቅ የሚናገሩትን አቶ ጌታቸው ረዳ በአደባባይ አወራው። የአማራውና የኦሮሞው አንድነት ደግሞ የበለጠ እየጠነከረ ሄደ።

በዚህ ወቅት ነው እንግዲህ የኢሰመጉ የምርመራ ቡድን ወደ ጊንጪ ያመራው። ጊንጪ አነስተኛ ከተማ ነች። ከከተማው ነዋሪ በላይ ከተማው በጦር ተሞልቷል። መከላከያ ሰራዊት፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የኦሮሚያ ልዩ ኃይል፣ የኦሮሚያ ፖሊስ፣ የአካባቢ ሚሊሻና ታጣቂ ከተማውን ወሮታል። መሳሪያ ያነገተ በየመንገዱ፣ በየሆቴሉ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ጤና ጣቢያ፣ ከተማ አስተዳደሩ፣ ወረዳ አስተዳደሩ ውስጥ ይርመሰመሳል። ይህ ሁሉ ኃይል በዚች ትንሽ ከተማ ለምን አስፈለገ ስንል ጠየቅን። መልሱ አጭር እና ቀላል ነበር። መላውን የኦሮሞ ህዝብ ከዳር እስከዳር ያነቃነቀው ህዝባዊ ተቃውሞ መነሻው ጊንጪ መሆኑን ተነገረን። ይህን የተቃውሞ ጧፍ መጀመሪያ ማን ለኮሰው ብለን ጠይቀን። የከተማው ነዋሪዎች በዝርዝር ተረኩልን። ዛሬ የምትመለከቱትን የትግል ጧፍ መጀመሪያ የለኮሱት የጊንጪ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ናቸው አሉን። አሁንም እንዴት በምን ምክንያት ብለንም ጠየቅን። በዝርዝር አስረዱን።

በአገሪቱ የተንሰራፋውን ሙስና፣ ሌብነት እና ዝርፊያ ተከትሎ የወረዳው ካቢኔና ባለስልጣናት የድርሻቸውን ሊዘርፉ ወደ ትምህርት ቤቱ ሄዱ። የትምህርት ቤቱን እግር ኳስ ሜዳ ቤት ሊሰሩበት እየመተሩ መከፋፈል ጀመሩ። "የልጆች መጫወቻ ሜዳ ላይ እንዴት ቤት ይሰራበታል?ልጆቹ ምን ላይ እየተጫወቱ ሊያድጉ ነው። እረፍት ሲወጡስ የት ሊያርፉ ነው"ብሎ አንድ መምህር ሲናገር ተማሪዎች ይሰማሉ። ወዲያውኑ ህፃናቶቹ ኳስ መጫወቻ ሜዳችን ኡ! ኡ! ኡ!ሲሉ ይጮሃሉ። ባለስልጣናቱ ያልጠበቁት ነገር ስለገጥማቸው ለጊዜው ያቆሙና ይቆጣሉ። ዳይሬክተሩን አስጠርተው ልጆቹ ወደየክፍላቸው ገብተው እንዲመከሩ መመሪያ ይሰጡና ይሄዳሉ። ዳይሬክተሩም መምህራኖቹም የተሰጠው መመሪያ ባይጥማቸውም ተማሪዎቹን ወደየክፍላቸው እስገብተው እንደ ነገሩ የደርጉና ያልፉታል።

የእለቱ ትምህረት ተጠናቆ ልጆች ወደ የቤታቸው ሲሄዱ ጩኸቱ ተሰምቶ ስለነበር ወላጆችና ታላላቆቻቸው ለምን ጮሃችሁ ሲሉ ይጠይቋቸዋል። የሆነውን ሁሉ ይናገራሉ። ደግ አደረጋችሁ።እንኳን ጮሃችሁ።አሁንም ደገምው ከመጡ ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ ጩሁ። እንዳትፈሩ እኛ በሩጫ እንደርስላችኋለን ሲሉ አበረቷቷቸው። ሁለት ሦስት አዘናግተው ሁሉም ተማሪዎች ክፍል መግባተቸውን ካረጋገጡ በኋል የወረዳውና የከተማው አስተዳደር ካቡኔዎችና ባለስልጣናት አሁንም በድጋሚ መጥተው ካቆሙበት ቦታ ጀምረው ሜዳውን መለካት ይጀምራሉ። በመስኮት የተመለከተ አንድ ተማሪ ሜዳችን ሜዳችን በማለት ጩኸቱን ያሰማል። ሁሉ ተማሪ ከክፍሉ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ ጩኸታቸውን ያቀለጡታል። ወላጆችና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ከመቅጽበት ትምህርት ቤቱን ይወራሉ። ባለስልጣናቱ ተደናግጠው በሩጫ ከአካባቢው ይሰወራሉ። የተሰበሰበው ሰልፍ መፈክር እያሰማ ከተማውን ያጥለቀልቃል። ወረዳ አስተዳደርና ከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት ድረስ በመሄድ ድርጊቱን ያወግዛል። ባለስልጣናቱም የተሰራውስህተት ነው ከእንግዲህ ወደዘህ ሜዳ የሚሄድ

ወደ ገጽ 10 የዞረ

ቃለ-መጠይቅ

“ ከዓላማው ማስፈጸሚያ ሥልቶች መካከል ለህብረተሰቡ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣ ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ማድረግ፣ በሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ የውትወታ ስራ መስራት፣ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ በፖሊስ ጣቢያዎችና በማረሚያ ቤቶች የእስረኞችን ሁኔታ ክትትል ማድረግ፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሲፈጸሙ ምርመራ በማካሄድና በማስረጃ የተደገፈ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማውጣት የመሳሰሉት ናቸው።

"የ30 ዓመታት ሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን እየመረመረ ሪፖርት የሚያወጣ ብቸኛ ድርጅት"

የዛሬው የመልዕክተ ኢሰመጉ አንግዳ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ/ኢሰመጉ/ ዋና ዳሬክተር የሆኑት አቶ ዳን ይርጋ ኃይሌ ናቸው፡፡ ኢሰመጉ ማነው? ለምን ዓላማ የተቋቋመ ደርጅት ነው? አሁን ያለበት ቁመና እንዴት ይገለጻል? ኢሰመጉ ከሌሎች ድርጅቶች በምን ይለያል? ኢሰመጉ ትምህርት ከመስጠትና ጥሰት ሲፈጸም ምርመራ አድረጎ መግለጫ ከማውጣት ውጭ ሌላ የሚያከናውነው ሥራስ ይኖራል? በሚሉና በሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ላይ ከባልደረባችን ብዙአየሁ ወንድሙ ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

ጥያቄ፡- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ/ኢሰመጉ/ ለብዙዎቹ እንግዳ ባይሆንም እንደመነሻ ኢሰመጉ ማነው? ለምን ዓላማ የተቋቋመ ነው? በሚለው በንጀምር።

አቶ ዳን ይርጋ፡- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ/ኢሰመጉ/ በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሠረት አገር በቀል ድርጅት ሆኖ በምዝገባ ቁጥር 1146 ከ02/11/11 ዓ.ም ጀምሮ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ዳግም ተመዝግቦ በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት ነው። ኢሰመጉ የተመሠረተው መስከረም 29 ቀን 1984 ዓ.ም.ነው። ኢሰመጉ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው። ዓላማውም በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግ ነው።

ከዓላማው ማስፈጸሚያ ሥልቶች መካከል ለህብረተሰቡ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣ ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ማድረግ፣ በሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ የውትወታ ስራ መስራት፣ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ በፖሊስ ጣቢያዎችና በማረሚያ ቤቶች የእስረኞችን ሁኔታ ክትትል ማድረግ፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሲፈጸሙ ምርመራ በማካሄድና በማስረጃ የተደገፈ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማውጣት የመሳሰሉት ናቸው።

ጥያቄ፡- ኢሰመጉ አሁን ያለበት ቁመና ወቅቱን የሚመጥን ሥራ ለመስራት የሚያስችለው ነው ማለት ይቻላል?

አቶ ዳን ይርጋ፡- አዎ ይቻላል። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ወቅቱን የሚመጥን ጠንከራና ተወዳዳሪ የሰብዓዊ መብቶች አስከባሪ ተቋም እንዲሆን በርከታ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ ተቋሙ ለሰራተኞቹና ለባለጉዳዮች የሚመች የስራ አካባቢ ለመፍጠር ይረዳ ዘንድ ቢሮዎችን የማደስ ስራ፣ የቢሮ ቁሳቁሶችን የመቀየር ስራ ተሰርቷል፣ የ5 ዓመት ስልታዊ እቅድ በባለሙያ በማሰራት በአዲሱ ዓመት እ.ኤ.አ.2022 ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል። በተጨማሪም የተለያዩ የውስጥ መመሪያዎችንና ፖሊሲዎችን በማዘጋጀት ወደ ስራ ተገብቷል። በተጨማሪም ኢሰመጉ በገለልተኛ አጥኚ ተቋም ባስጠናው መሰረት የኢሰመጉን መዋቅር (structure)፣ የስራ መደልድልና ተያያዥ የሆኑ በርካታ ኢሰመጉን የሚያጠናክሩ ስራዎችን በማከናወን ላይ እንገኛለን። ይህም የኢሰመጉን የሥራ አቅም እንደሚያጠናክር ይታመናል።

ጥያቄ፡- በአገራችን በተከሰተው የሪፎርም ለውጥ ተጠቅመው በርካታ

“ በተጨማሪም ኢሰመጉ በገለልተኛ አጥኚ ተቋም ባስጠናው መሰረት የኢሰመጉን መዋቅር (structure)፣ የስራ መደልድልና ተያያዥ የሆኑ በርካታ ኢሰመጉን የሚያጠናክሩ ስራዎችን በማከናወን ላይ እንገኛለን። ይህም የኢሰመጉን የሥራ አቅም እንደሚያጠናክር ይታመናል።

ቃለ-መጠይቅ

አዳዲስ መሰል ድርጅቶች (csos) ተቋቁመዋል፡፡ የእነዚህ ድርጅቶች መቋቋም በኢሰመጉ ላይ የሚያመጡት ተጽእኖ ይኖር ይሆን?

አቶ ዳን ይርጋ፡- እንደሚታወቀው በአሁኑ ወቅት በርካታ የሲቪል ማህበረሰብ (csos) ተቋማት በባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ተመዝግበው 3000 ያህሉ ወደ ስራ እንደገቡ የሚታወቅ ጉዳይ ነው።የእነዚህ ድርጅቶች መመስረት በኢሰመጉ ልዕለ ሥራዎች ላይ በቀጥታ የሚያመጣው ተጽዕኖ የለም። ይሁንና ተመሳሳይ ሥራን በተመሳሳይ ቦታዎች መስራት ላይ ግን የሀብት ብክነት እንደሚያመጣ በማወቅ በመናበብና በተቀናጀ መልኩ ተደራሽ ባልሆኑ ቦታዎች ላይ መስራት እንደሚገባው ኢሰመጉ ያምናል።

ኢሰመጉ ወቅቱን የሚመጥን ተቋም ለማድረግ ስራዎች አስቀድሞ ስለተሰሩ በኢሰመጉ ላይ የሚያደርሰው ጫና አይኖርም። ምክንያቱም በህዝብ፣ በአጋሮችና በለጋሾች ዘንድ መልካም ስም ያለው ተቋም በመሆኑ ይህንን በጎ ጎን በይበልጥ ማጠናከር ላይ ርብርብ እያደረግን እንገኛለን።

ጥያቄ፡- ኢሰመጉ ባለው በጀትና የሰው ኃይል ወቅቱ የሚጠይቀውን ሥራ ለመስራት የሚመጥን ቁመና ላይ ነውን?

አቶ ዳን ይርጋ፡- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) በዚህ ወቅት ለስራ እንቅስቃሴ የሚያስፈልገው የበጀትና የሰው ሀይል አለው። ይሁንና ስራዎቹን የበለጠ ለማስፋፋትና የሰው ሀይሉንም የበለጠ ለማስፋትና የሰው ኃይሉንም የበለጠ በየዘርፉ

ኢሰመጉ ወቅቱን የሚመጥን ተቋም ለማድረግ ስራዎች አስቀድሞ ስለተሰሩ በኢሰመጉ ላይ የሚያደርሰው ጫና አይኖርም። ምክንያቱም በህዝብ፣ በአጋሮችና በለጋሾች ዘንድ መልካም ስም ያለው ተቋም በመሆኑ ይህንን በጎ ጎን በይበልጥ ማጠናከር ላይ ርብርብ እያደረግን እንገኛለን።

መጨመር አስፈላጊ ስለሆነ በዚሁ ረገድ ይህንን የበለጠ ለማጠናከርና ለማስፋት በርካታ ተግባራትን እያከናወንን (እየሰራን) እንገኛለን። ይህንንም ስራ ገቢራዊ ለማድረግ ኢሰመጉ በአሁኑ ጊዜ ባሉት 8 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹንም ባማከለ መልኩ እየሰራ ይገኛል።

ጥያቄ፡-ኢሰመጉን ከሌሎች መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ልዩ የሚያደርገው ምንድ ነው?

አቶ ዳን ይርጋ፡- ኢሰመጉን ከሌሎች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ልዩ የሚያደርጉት በርካታ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ፡- በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት መሆኑ፣ ባለፉት 30 ዓመታት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን እየመረመረ ሪፖርት የሚያወጣ ብቸኛ ድርጅት መሆኑ፣ በአባላት የተመሰረተና በሁሉም የሀገራችን አካባቢዎች ንቁ አባላት ያሉት ተቋም መሆኑ፣ በአሁኑ ወቅት ባሉት ስምንት (8) ቅ/ጽ/ቤቶች ሰፊ የሰብዓዊ መብቶች የማስከበር ሥራ፣ የህግ የበላይነትና ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ የበኩሉን ሰፊ ድርሻ እየተወጣ ያለ ተቋም መሆኑ፣ በቅርቡም የተካሄደው 6ኛው አገር አቀፍ ምርጫን የመራጮች ትምህርት በመስጠት፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የምርጫ ክርክር መድረክ በማዘጋጀት፣ የምርጫ መታዘብ ሥራዎችን ለብቻው በመሥራት አቅም እንዳለው ማሳየቱ ከብዙ በጥቂቱ የሚጠቀሱ ናቸው።

ጥያቄ፡- በተለያዩ ጊዜያት በመንግስት አካላትና በሌሎች ኃይሎች የተፈጸሙ ልዩ ልዩ የመብት ጥሰቶችን እየመረመረ መደበኛና ልዩ መግለጫዎችን እንዲሁም በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫ ከማውጣት ወጭ ሌላ የምታከናውንት ሥራ ይኖራል?

አቶ ዳን ይርጋ፡- ኢሰመጉ በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶችን በቅርብ እየተከታተለ ከሚያወጣቸው መግለጫዎች ውስጥ መደበኛ መግለጫ፣ ልዩ መግለጫ እና ጋዜጣዊ መግለጫ ይገኙበታል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በየዕለቱ የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶችን አዲስ አበባን ጨምሮ ካሉት ቅ/ጽ/ቤቶች እና አባላቱ እንዲሁም በሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ደጋፊዎቹ ክትትልና ሪፖርት በየሳምንቱ የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታን በቅርብና በትኩ

ከምርመራ ማህደራችን

> “ የኢሕአዴግ መፍረስ እና አዲሱ የብልጽግና ፓርቲ መመስረትን፤ እንዲሁም በኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝን ምክንያት በ2012 ዓ.ም ነሃሴ ወር ላይ ሊደረግ ታስቦ የነበረው ሐገር አቀፍ ምርጫ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ መራዘሙን ተከትሎ አለመግባባቱ እና መካረሩ የበለጠ እየሰፋ ስለመሄዱ ግልጽ ነበር።

ማይካድራ የዘመናችን ኦችዝም?

ይህ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ ቀዳሚ ትኩረቱን ጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም በወቅቱ ስልጣን ላይ በነበረው የትግራይ ክልል መንግሥት እና በፌዴራል መንግሥት መካከል ጦርነት መጀመሩን ተከትሎ፣ በትግራይ ክልል፣ ምዕራባዊ ዞን፣ ማይካድራ ከተማ እና አካባቢው ላይ ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም የተፈጸመውን ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መለየት ላይ ነው። የተፈጸመው የሰብዓዊ መብት ጥሰት መጠን እጅግ ሰፊ በመሆኑ፣ ይህ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ዘገባ የኢሰመጉ የመስክ ምርመራ ዐቅም እና በአካባቢው የነበረው የጸጥታ ሁኔታ በፈቀደው ልክ በዋናነት መሠረታዊ የሚባሉትን የመብት ጥሰቶች አካቷል። ልዩ ዘገባው የተዘጋጀው የኢሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ምርመራ ባለሙያዎች ከህዳር 24 - ታህሳስ 2 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ በማይካድራ፣ ሁመራ፣ አብደራፊ፣ አብርሃጅራ፣ ዳንሻ እና ጎንደር አካባቢዎች ለመስክ ምርመራ ሥራ በተሰማሩበት ወቅት ባደረጉት ምልከታ፣ ባሰባሰቡት የድምጽ፣ የፎቶ እና የቪዲዮ መረጃና ማስረጃዎች መሠረት ነው።

የምርመራ ቡድኑ በተጠቀሱት አካባቢዎች ተዘዋውሮ የሟች ቤተሰቦችን፣ በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን፣ የዓይን ምስክሮችን፣ የቀብር ስርዓቶችን ያከናወኑ ሰዎችንና የቤተ-ክርስትያን አባቶችን፣ በጊዜያዊነት የተቋቋሙ የመንግሥት ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችንና ሌሎችም የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሞ ልዩ ልዩ መረጃዎችን እና ማስረጃዎችን አሰባስቧል። ከእዚህ በተጨማሪ፤ ቡድኑ በቤተ-ክርስቲያን ውስጥ እና ከቤተ-ክርስቲያን ቅጥር ውጪ የሚገኙ የጅምላ መቃብሮችን ተዘዋውሮ የጎበኘ ሲሆን፤ በወቅቱ ያልተነሱ እና የቀብር ስርዓት ያልተፈጸመላቸው አስከሬኖችን ጭምር አግኝቷል። የኢሰመጉ መርማሪዎች ተጎጂዎችን በአካል በማግኘት ያነጋግሩ ሲሆን፤ የአካባቢው የመንግሥት ኃላፊዎችን፣ የህክምና ተቋማትን አነጋግረዋል፤ መረጃዎችንም ወስደዋል። የዚህ ዘገባ የምርመራ ሥራ በሚከናወንበት ወቅት ኢሰመጉ የሚከተሉት ዋና ዋና ውስንነቶች እና ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፡-ኢሰመጉ ያለበት የገንዘብ፣ የሰው ኃይል፣ ለምርመራ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች እጥረት፤በወቅቱ በአካባቢው በነበረው የጸጥታ ስጋት የተነሳ ከፍተኛ የሆነ የትራንስፖርት እጥረት በመኖሩ የኢሰመጉ መርማሪዎች እንደልብ ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ እና ተጎጂዎችን እና የተጎጂ ቤተሰቦችን ለማናገር መቸገር፤ዓለም አቀፉ የኮሮና ቫይረስ አደገኛ ሥርጭት፣ የኢሰመጉ መርማሪዎችን ከቦታ ቦታ የመዘዋወር እና የመሥራት አቅም የገደበ መሆኑ፤በምርመራ ሥራው በተሸፈኑት አካባቢዎች የተፈጸመው የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የደረሰው ሰብዓዊ ቀውስ ከኢሰመጉ የማጣራት አቅም በላይ መብዛቱ፤ተጎጂዎች እና የተጎጂ ቤተሰቦች በነበረባቸው የፍርኃት ስሜት የተነሳ ቃላቸውን በነጻነት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው፤በወቅቱ በተፈጸመው ድርጊት የደረሰውን አጠቃላይ ጉዳት አስመልክቶ ያላቸውን መረጃ እንዲሰጡ የተጠየቁ በየደረጃው ያሉ የህክምና፣ የኃይማኖት እና የፍትሕ ተቋማት መዋቅራቸው ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የፈረሰ በመሆኑ መረጃና ማስረጃዎችን ለማግኘት መቸገር የሚሉት ይጠቀሳሉ።

ጠቅላይ ሚንስትር ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር) ወደ ሥልጣን ከመጡበት መጋቢት 2010 ዓ.ም ወዲህ፤ እርሳቸው የሚመሩት መንግሥት የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝ ሁኔታ ከቀድሞ የተሻለ ለማድረግ በርካታ እርምጃዎችን መውሰዱ ይታወቃል። ይሁንና፤ በሐገሪቱ ያለው የፖለቲካ ልዩነቶች መካረር እና የብሔር ጽንፈኝነት የእርስ በእርስ ግጭቶች፣ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች እና እጅግ የከፉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንዲፈጸሙ ምክንያት ሆኗል፡ ፡ በዚህም ምክንያት የሰዎች ሕይወት ጠፍቷል፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ውድመት ደርሷል፣ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ደግሞ ከመኖሪያ ቤታቸው ተፈናቅለው ለብዙ መከራና ስቃይ ተዳርገዋል።

ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ከነበሩት ፖለቲካዊ ልዩነቶች መካከል በፌዴራል መንግሥት እና በትግራይ ክልል መንግሥት መካከል የነበረው ከፍተኛ የሆነ አለመስማማት ዋነኛው ነው። የጠቅላይ ሚንስትር ዐብይ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣበት ጊዜ አንስቶ ከክልሉ አስተዳደር ጋር አለመግባባት ስለመኖሩ የሚያስረዱ ንግግሮች በሁለቱም አካላት በግልጽ ይነገሩ እንደነበር አይዘነጋም። በተለይም የኢሕአዴግ መፍረስ እና አዲሱ የብልጽግና ፓርቲ መመስረትን፤ እንዲሁም በኮሮና ቫይረስ ወረርሺኝን ምክንያት በ2012 ዓ.ም ነሃሴ ወር ላይ ሊደረግ ታስቦ የነበረው ሐገር አቀፍ ምርጫ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ መራዘሙን ተከትሎ አለመግባባቱ እና መካረሩ የበለጠ እየሰፋ ስለመሄዱ ግልጽ ነበር።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ምርጫው መራዘሙን ይፋ ማድረጉን ተከትሎ፤ የትግራይ ክልል መንግሥት ምርጫ ለማድረግ በማሰብ የሕግ ማሻሻያን ጨምሮ የምርጫ አስፈጻሚ ተቋም ማቋቋምን የመሳሰሉ እርምጃዎችን ወስዷል። የፌዴሬሽን ምክር ቤት በበኩሉ ነሃሴ 30 ቀን 2012 ዓ.ም <<…የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት፣ አስፈጻሚ አካላት እና ምርጫ ኮሚሽን ምርጫን በሚመለከት ያወጣው አዋጅ፣ ያሳለፏቸው ውሳኔዎች እና የፈጸሟቸው ተግባራት ከሕገ-መንግሥቱ ጋር የሚቃረኑ በመሆናቸው እንዳልተደረጉ የሚቆጠሩ፣ የማይጸኑ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ናቸው…>> የሚል ውሳኔ አሳልፏል። ጉዳዩ በዚህ ደረጃ ላይ እያለ በክልል ደረጃ ሊደረግ የታሰበው ምርጫ ጳጉሜን 4 ቀን 2012 ዓ.ም ተደርጓል።

ከምርጫው መደረግ ማግስት በሁለቱም ወገኖች

ወደ ገጽ 11 የዞረ

“ በመሰረተ ሀሳብ ደረጃ ሰብአዊ መብቶች ስንል ሰጭ እና ነሽ በሌለበት ሁኔታ የሁሉም የሰው ልጆች መለያ ሀብቶች መሆናቸውን የጋራ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል። በዚህም መሰረት የሰው ልጅ መሠረታ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ናቸው ተብለው ዓለም-አቀፍ ዕውቅና ከአገኙት ውስጥ የሚከተሉትን በዋናነት መጥቀስ ይቻላል።

ሰብዓዊ መብቶች

ደረጀ መላኩ

መግቢያ

እንደሚታወቀው ሁሉ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት መቋቋምም ሆነ የሰብዓዊ መብቶች በስፋት ተግባራዊ የመሆናቸው አስፈላጊነት በዓለም ኅብረተሰብ ውስጥ በይበልጥ ትኩረት ያገኘው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሕዝቦች ላይ ያስከተለው ከባድ ጥፋትና እልቂት በመሆኑና ይህም ዓይነት ጉዳት በተቻለ መጠን ወደፊት እንዳይከሰትታልሞ የተባበሩት መንግስታት ቻርተር በመግቢያው ላይ እና እንዲሁም በአንቀጽ 1 (3)፣55 እና 56 ውስጥ ሰብዓዊ መብቶች ለሰው ልጅ ሁሉ ጥቅም ያለምንም ልዩነት ተግባራዊ የሚሆኑበትን ዘዴ ሁሉ ማጠናከር አስፈላጊ መሆኑን ከብዙዎቹ ድርጅቱ ዓለማዎች መካከል አቢይ ትኩረት እንዲሰጠው ያደረገበት የድርጊቱ ፕሮግራም ከተቀየሰ 75 ዓመታት ሊሆነው ነው።

በዚህም የተ.መ.ድ. የድርጊትፕሮግራም መሠረት እንደ እ.ኤ.አ.በታህሣሥ 1948 ዓ.ም. 30 አንቀጾች ያሉት የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ ታወጀ።

ይህም ዓለም አቀፍ ድንጋጌ በታወጀ በ48 ዓመታት ግዜ ውስጥ እ.ኤ.አ እስከ ጥር 1996 ዓ.ም. ድረስ በተ.መ.ድ አማካይነትበተለያዩ አርእስተ ጉዳዮች ላይ የአተኮሩ የሰብዓዊ መብቶች የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች፣ኮንቬንሽኖችና ፕሮቶኮሎች ብዘት ከአንድ መቶ በላይ የደረሰ ሲሆን ከነዚሁ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ ኢትዮጵያ 26ቱን (25 ፐርሰንቱን) ያጸደቀች በመሆንዋ ስምምነቶችን በመቀበል የቃል ገጽታ በብዛት ከገቡት ጥቂት ሀገሮች መካከል በመጀመሪያው ረድፍ ውስጥ መገኘቷ ሲጤን ቃልን ከተግባር ጋር ከማዋሃድ አስፈላጊነት አንጻር ሀገሪቱ የገባቻቸው ግዴታዎች በቀላሉ የሚታዩ አይሆንም።

ኢትዮጵያዊነትና ሰብአዊ መብቶች

ኢትዮጵያዊነት ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያለምንም መሰረታዊ ልዩነት በሚመለከት መልኩ፡-

- ሰብአዊነቱ ከተረጋገጠ ማንነት
- ከብሔራዊ አንድነትና ነጻነት
- ከሕግ ልዕልና እና የሕግ የበላይነት
- ከዲሞክራሲያዊነት
- በሕግ ፊት ከሚረጋገጥ እኩልነት
- በሀገሪቱ ውስጥ በአለውም የተፈጥሮ ሀብት ተጠቃሚ ከመሆን ጥያቄዎችና በአጠቃላይ፣ በሀገሪቱ ሕገ መንግስትም ሆነ መንግስት ወዶና ለምዶ በተቀበላቸው ዓለም-አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ጥያቄዎች ተግባራዊነት ውጭ ኢትዮጵያዊነት የተሟላ ትርጉም ሊኖረው አይችልም።

የሰብዓዊ መብቶች ይዘት

ሰብአዊ መብት ስንል ምን ማለታችን ነው ?

የሰብአዊ መብቶች ዝርዝር እ.ኤ.አ. በዲሴምበር 1948 ዓ.ም. የተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ ብሎ በአጸደቀው ዓለም-አቀፍ ሰነድ ውስጥ የተካተቱ ሲሆን ሰነዱንም በድርጅቱ ውሳኔ (ሪዞልዩሽን) መልኩ ኢትዮጵያ በድርጅቱ መሥራ አባልቷ ምክንያት ተቀብላው ከኖረች በኋላ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግስትም ለወቅቱ ህገመንግሥት ሆኖ እንዲያገለግል በአዘጋጀው ቻርተር አማካይነት እንደ እ.ኤ.አ. ከ1991 ሐምሌ ጀምሮ ከላይ የተጠቀሰውን የተ.መ.ድ. የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ በግልጽ የኢትዮጵያ ከፍተኛው የሕግ አካል አድርጎ ተቀብሎታል፡፡ እንዲሁም ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ አገላለጽ ሰብአዊ መብቶች ነኢ..ፌ.ዴ.ሪ. መንግሥት አዲስ ሕገ መንግሥት ውስጥ በ30 አንቀጾች አማካይነት እንደገና ተዘርዝረው መገኘታቸው የእነዚህ መብቶች መኖርተግባራዊነታቸው ከአስከተለው ችግር ሌላ ጥያቄ የለበትም።

በመሰረተ ሀሳብ ደረጃ ሰብአዊ መብቶች ስንል ሰጭ እና ነሽ በሌለበት ሁኔታ የሁሉም የሰው ልጆች መለያ ሀብቶች መሆናቸውን የጋራ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት የሰው ልጅ መሠረታ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ናቸው ተብለው ዓለም-አቀፍ ዕውቅና ከአገኙት ውስጥ የሚከተሉትን በዋናነት መጥቀስ ይቻላል።

- የሰብአዊ መብቶች ጆርናል ቅጽ 17 ቁጥር 1 እና 2 ፣ የጥር 1996 እትም፣
- ሁሉም ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች በ4 ዋና ዋና ክፍሎች፣
- በሕግ ፊት ሰው ሆኖ የመታወቅ መብት፣
- በሕግ ፊት እንደ ሰው መቆጠር፣
- በሕይወት የመኖር መብት፣
- በሕግ ፊት የእኩልነት መብት፣ የአካል ደህንነት የመከበር መብት፣
- በዘፈቀደ (ያለ ሕጋዊ ሥርዓት) ያለመያዝና ያለመታሰር መብት፣
- የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት፣
- የእምነትና የሕሊና እንዲሁም ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፣
- የመሰብሰብና በማኅበር የመደራጀት መብት፣
- ከቦታ ቦታ የመዘዋወርና በመረጡት ቦታ የመኖር መብት፣
- ጉዳዩን ለፍርድ ቤትና ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ፍትሕ የማግኘት መብት
- የመሥራትና በሀገሪቱ ሀብት የመጠቀም መብት፣
- የዜግነት መብት፣
- የባለ ንብረትነት መብትና፣
- የመምረጥና የመመረጥ መብት የመሳሰሉት ይገኙበታል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትም ሆነ ያልተጠቀሱት የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች አስቅድሞ እንደተጠቀሰው በኢ..ፌ.ዲ..ሪ. መንግሥት ሕገ መንግሥትና በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ተግባራዊ አደርጋቸዋለሁ ብሎ በተቀበላቸው የተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ፣ ዓለም-አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት ውስጥ በዝርዝር የሚገኙ የኢትዮጵያ የህግ አካ ሲሆኑ፣ እያንዳንዱን የሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ይዘት በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ መዳሰስ ፈጽሞ የማይቻል መሆኑን ለአንባቢያን በቅድሚያ እገልጻለሁ።

እንዲሁም በኢትዮጵያ ስለ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ ወይም ፖለቲካዊ መብቶች የወቅቱ ሁኔታ የተወሰነ ግንዛቤ ወይም አስተያየት ከመስጠቴ በፊት፣ ማኅበራዊ ችግሮች ሁሉ የተወገዱበትና ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችም ሙሉ በሙሉ የተከበሩበት አገር ወይም የዓለም ክፍል አለመኖሩ የታወቀ ቢሆንም፣ በአብዛኛው የአፍሪቃ አህጉር ውስጥም ሆነ በተለይ በሀገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ የችግሮቹ ዓይነትም ሆነ ውስብስብነት ግን የሚታይ፣የሚዳሰስ ስለመሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ስለመሆኑ የሚከራከር ይኖር ይሆን ? ካለም ሀሳብን በሃሳብ መሞገቱ አስተማሪ ሊሆን ይቻለዋል።

ቀጣይ ክፍል 2 በመጪው ወር ይቀጥላል

መዝናኛ

የደም ግፊት መጠን መጨመር

< ጌትዬ ! > አሉኝ የሚያሳዝኑ አዛውንት በሞጨሞጩ አይኖች ወደላይ ቀና ብለው እያስተዋሉኝ። ድምፃቸው ይርገበገባል። እድሜያቸውን ሙሉ ደም ሲረጩ የኖሩት የደም ስሮች በአይበሉባዎቻቸው ላይ እንደ ድር ተጠላልፈዋል።

ባንክ ውስጥ ነኝ።

እየፃፍኩ ካለሁበት ቀና ብዬ አዛውንቷን አስተዋልኳቸው። ከፊቴ ቆመው ያስተውሉኛል።

< ምን ልርዳዎት እማማ ! > አልኩ በትህትና።

ከአንድ ጎናቸው ዘምበል ብለው፣ ድምፃቸውን ዘለግ አደረጉና <ጆሮዬ ያጠራጥረኛል ! > ፈገግ እያሉ። (ፈገግ ያሉ የመሠለኝ ከአፍ መሸፈኛ ጭምብላቸው ስር የተሸበሸበ የፊት ቆዳቸው ወደ አይኖቻቸው ደመና ስር ሲሰበሰብ ስላየሁ ነው።)

አካባቢዬን ቃኘሁና ድምፄን ከፍ አድርጌ < ምን ላግዝዎት እማማ? ! > አልኩ።

ከደረታቸው ስር የባንክ ደብተር እያወጡ < ወጪ ፃፍልኝ ! > አሉ።

ደብተሩን ተቀብዬ፣ ገለጥ አድርጌ ስምና የአካውንት ቁጥራቸውን አይቼ መፃፍ ጀመርኩ።

<ስንት ብር ልፃፍ?>

<10 ብር >

ቀና ብዬ አየኋቸው ። ማስኬን ወረድ አረኩና ጮክ ብዬ <አስር ብር አሉኝ?> አልኩ ለማረጋገጥ።

<አስር ብር ልጄ። ብዙ ካወጣሁ ይጠፋብኛል። ለቡና ብቻ ነው። ነገ ከነገ ወዲያ ደሞ መጥቼ አወጣለሁ።>

<አስር ብር ብቻ >ብዬ ፃፍኩና < ይፈርማሉ?> ስል ጠየኩ።

የተጣመመች አውራ ጣት አሳዩኝ። ገባኝ። ደረሰኙን ከደብተራቸው ውስጥ ከትቼና እንዲከተሉኝ ምልክት አሳይቼ ወደ መስኮቱ አቀናን። ለከፋይዋ የእርሳቸውን እንድታስቀድም ነግሬ ሰጠኋት።

ወረቀቱን እያየች ስማቸውን ጠራችና ጮክ ብላ <እማማ . . . ስንት ቀን ልንገርዎት? አስር ብር ማውጣት አይቻልም። ዝቅተኛ 25 ይፃፉ ከዛ በታች አይቻልም። >

የተናደዱ መሠለኝ። እጃቸው እየተንቀጠቀጠ <የምፈልገው 10 ብር ነዋ፡ ፡ አልበዛምንዴ ! 10 ብር ስጪኝ። ቆጥቤ ነው የምጠቀመው ምን አገባሽ? እንዲ ናትና ሒሩት አስፋው ! ሁሉን በልቼ በምኔ ልጦርልሽ ነው?>

<እንግዲ ጀመሩ ልጅ የለኝ ምናምን ሊሉ ነው . . > አለች ልጅቱ በለሆሳስ።

< . . .እኔ የሚጦር ልጅ የለኝ ቆጥቤ ነው ጡረታዬን የምጠቀመው።>

< እማማ 20ሺ ብር አለዎትኮ ! >

<ምን አገባሽ ብሽቅ ! 10ብሬን አምጪ . . .>

እኔ ምን እንደምል ግራ ገባኝ። 10ብር ልሰጣቸውም አሰብኩ።

<ስንት ማውጣት ይቻላል?> አሏት።

<ካለዎት በቀን 50ሺ ይችላሉ። አለችና ፈገገች። በረዶ የመሠሉ ጥርሶቿን አየኋቸው።

< ዋ ! . . . ቁንጅና ረጋፊ ነው። > አሉ አተኩረው እያስተዋሏት።

ፈገግ ብዬ ለመጀመሪያ ግዜ ቲማቲም የመሠለ ጉንጭ ያላትን ቆንጆ በደንብ አየኋት። መናደድ ጀምራ ነበር።

<ፈረደብኝኮ . . . ለምንድነው ደሞ ሁሌ እኔጋ የሚመጡት? ከራሴ ልስጥዎት ስላቸው ይሳደባሉ።>

ጮክ ብላ < ይግቡና አለቃውን ያናግሩ . . .> ብላ ደብተራቸውን ገፋችላቸው። የ'ኔን ወረቀት አንስታ የፊደል ሰሌዳዋን መደብደብ ጀመረች። ራቅ ብለው በአንክሮ ያስተውሏት ጀመር። አልተነቃነቁም።

<ለምን ይሆን ሁሌ አንቺጋ የሚደርሰኝ? ዋ እቴ ! ቁንጅና እንደ ንፋስ ያልፋል ! . . . . በገዛ ገንዘቤ ከመለመን እዚሁ ብሞት ይሻለኛል ! > አሉ በምሬት።

<እዚሁ ብሞት ይሻለኛል? ! > ሲሉ ምን ትዝ አለኝ? (እዚሁ እንዴት ሊሞቱ ይችላሉ ብዬ እያሠብኩ !)

ትዝ ያለኝ ስለ ጋዜጠኛ ክርስቲን የሠማሁት ነበር።

ክርስቲን ቸብበክ አሜሪካ ውስጥ የቲቪ ጋዜጠኛ ነበረች። በ1974 አንድ ቀን የቀጥታ ስራ እየሠራች በሚያምር ድምጿ ድንገት እንዲህ አለች።

" . . . . በጣቢያችን የብሮድካስት ህግ መሠረት ምንም አይነት አሳዛኝና አስፈሪ ነገሮች እንደወረዱ እናቀርባለን። እናም የተከበራችሁ ተመልካቾች ዛሬ በታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ የተላለፈ ራስን የማጥፋት ሒደት በቀጥታ ታያላችሁ . . . "

እናም ሪቮልቨር ሽጉጧን ላጥ አድርጋ ጭንቅላቷ ላይ ምላጩን ሳበች።

ከዚያ ወዲህ እንዲህ ላይቭ የተላለፈ አስደንጋጭ ክስተት መኖሩን እንጃ።

ጤና

ያ ሁነት ግን በታሪክ የመጀመሪያ ነው።

ብሬን ተቀብዬ ልወጣ ስወዛገብ በድጋሚ ጠሩኝና <ወጪ ፃፍልኝ!> አሉኝ።

ግራ ገባኝ።

<20ሺ ወጪ ብለህ ፃፍልኝ!> አሉ በርግጠኝነት።

እየተጠራጠርኩ ለሰከንዶች አስተዋልኳቸውና መፃፍ ጀመርኩ። ደሞ ቀና ብዬ አየኋቸው። ልክ ነው! በሚል አዎንታ ጭንቅላታቸውን ላይታች አወዛወዙ።

በብስጭት ሁሉንም ብር ሙልጭ ሊያረጉት ነው ስል አሰብኩና ፈገግ አልኩ። ሁሌ ከመጨቃጨቅ ሳይሻል አይቀርም። ፃፍኩና ሰጥቻቸው ልወጣ ስል <ቆይ ልጄ!> አሉና እጄን ያዝ አደረጉኝ። እኔ ጭቅጭቃቸውን ላለማየት ወጥቼ ልሰወር ነበር ሀሳቤ።

<ሌላ ፃፍልኝ! ...>

ከአፋቸው ነጠቅ አድርጌ < እማማ ሁሉንም ፃፍኩትኮ ...!> አልኩ እየፈገግኩ።

< ... አደለም ልጄ! 10 ብሯን ቀንስና ሌላውን አስገባልኝ። ለቀረው ማስገቢያ ፃፍልኝ ።>

በመገረም አፌን ከፈት አድርጌ አስተዋልኳቸውና ነገሩን መልሼ አሰብኩት። ይቻላል።

የገቢ ደሰሠኙን ሳብ አድርጌ መፃፍ ጀመርኩ።

ገቢ 19,990.00

ፃፍኩና ወረቀቱን ፈገግ ብዬ አቀበልኳቸው።

ሙጭሙጭ ባሉ አይኖች የጠቀሡኝ መሰለኝ። በርግጠኝነት ሴትየዋ ጠቅሰውኛል። ተጠራጥሬ አፍጥጬ ሳይ ወረቀታቸውን ይዘው እየተወዛወዙ ወደመስኮቱ አቀኑ።

እኔም አየሩ ላይ ጥቅሻውን ደጋግሜ እያየሁ ፈዘዝኩ ደግሞም ሌላ ጭቅጭቅ ላለመስማት ቶሎ መውጣት ነበረብኝ። <ግንኮ መብታቸው ነው!> እያልኩ እያሰብኩ።

/ ሌላ ቦታ በእንግሊዝኛ የሚመስል ነገር አንብባችሁ ከነበር አትጨነቁ ልክ ናችሁ። ምናብና ምንባብ ማለት እንደዛ ነው /

ዐብይ ተስፋዬ ምናብና ምንባብ ብሎ እንደፃፈው

የደም ግፊት መጠን መጨመር

የደም ግፊት መጨመር በሽታ ምን ያህል ትኩረት እንሰጠዋለን አንዳንዴ ባለማስተዋል ቀላል የሚመስሉ ነገሮች አደጋ ላይ ሊጥሉን ይችላሉ ይህንን ለማስገንዘብ እና ምን ስናደርግ ልንጋለጥ እንችላለን የሚለውን እንመለከታለን እነሆ፡ -

የደም ግፊት የሚገለፀው በደም ቅዳ ውስጥ ልብ የምትረጨው የደም መጠን (ብዛት) እና የሚቋቋመው የደም መጠን ተመጣጣኝ መሆን ሲሆን የደም ግፊት መጨመር ማለት ደግሞ ልብ የምትረጨው ደም መብዛት እና የደም ቅዳ ቱቦ (Arteries) መጥበብ ማለት ነው።

የደም ግፊት መጨመር ምልክቶችን ሳያሳይ ለረጅም ጊዜ አብሮን ሊቆይ ይችላል። ነገር ግን የደም ግፊቱ ከቁጥጥር ውጪ ሲሆን አደጋ ላይ ሊጥለን ይችላል።

ምልክቶቹ፡- አንዳንዶቹ የደም ግፊት መጠን ጨምሮ ምልክቶችን ላያሳይ ይችላሉ።

ራስ ምታት

የትንፋሽ ማጠር

የአፍንጫ መድማት (ነስር)

መንስኤዎች

የደም ግፊት መጨመር ሁለት አይነት ናቸው

1.የመጀመሪያው የደም ግፊት መጠን መጨመር

ብዙ ጊዜ ምክንያቱ አይታወቅም ነገር ግን በብዙ ዓመታት እያደገ የሚመጣ እና የሚጨምር ነው።

2.ሁለተኛው የደም ግፊት መጠን መጨመር

ይህኛው መነሻ ምክንያት ያለው ሲሆን ድንገት የሚከሰት እና መድሀኒት እንዲጀምር ምክንያት ሊሆን ይችላል።

የኩላሊት ችግር ካለ

የታይሮይድ ችግር ካለ የደም ስር ላይ ከውልደት ጀምሮ ችግር ካለ

አንዳንድ መድሀኒቶች፡- (የእርግዝና መከላከያ፣ ቀዝቃዛ ነገሮች፣ ከመጠን በላይ ማስታገሻ መድሀኒቶችን መጠቀም)

አደንዛዥ እፅ

የአልኮል መጠጦች

አጋለጭ ሁኔታ

፣እድሜ (ለወንድ 45 ፣ ለሴት 65)

ከቤተሰብ የታመመ ካለ

ከመጠን ያለፈ ክብደት

እንቅስቃሴ አለማድረግ

ቶባኮ መጠቀም (ማጨስ)

ከመጠን በላይ ጨው መጠቀም

የምግብ ስርዓት ላይ የፖታሲየም እጥረት መኖር

የአልኮል መጠጥ በጣም ተጠቃሚ መሆን

ጭንቀት

የኩላሊት ህመም

የስኳር ህመም

ምርመራ

በደም ግፊት መለኪያ መሳሪያ ክንድ ላይ መለካት

የደም ግፊት ልኬቱን የምናነበው በሚሊሜትር ሜሪኩሪ ነው። የደም ግፊትን በአራት እንከፍለዋለን

1.ትክክለኛ(ጤናማ)የደም ግፊት መጠን 120/80mmHg

2. የደም ግፊት ከመከሰቱ በፊት የምናስተውለው መጠን የላይኛው(systolic)ከ120 እስከ 139 mmHg እና የታችኛው(diastolic)ከ80 እስከ 89 mmHg ሲሆን ፕሪሀይፐርቴሽን(prehypertension) እንለዋለን በጊዜ ሂደትም አደገኛ የመሆን ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡

3.የመጀመሪያ ደረጃ የደም ግፊት የላይኛው(systolic)ከ140 እስከ 159 mmHg እና የታችኛው(diastolic)ከ90 እስከ 99 mmHg ሲሆን

4.ሁለተኛው ደረጃ ደም ግፊት ይህኛው አደገኛ የደም ግፊት ደረጃ ነው።

የላይኛው(systolic)160 mmHg እና ከዛ በላይ እና የታችኛው(diastolic) 100 mmHg እና ከዛ በላይ ሲሆን ህክምናው በየደረጃው ይለያያል የደም ግፊት መጠን ከመጨመሩ በፊት የምናስተውለው የደም ግፊት መጠን መጨመር የአኗኗር ዘይቤን በመቀየር ይስተካከላል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ የደም ግፊት ግን እንደየአስፈላጊነቱ መድሀኒት እንዲጀመር ይደረጋል። ለምሳሌ፡ -

ሽንት የሚያሸኑ መድሀኒቶች

የደም ስርን የሚለጥጥ ወይም የሚያሰፋ መድሀኒት

የደም ስር ጡንቻ የሚያላላ(relax)

የአኗኗር ዘይቤን መቀየር

የምግብ ስርዓት ላይ ጨው መቀነስ

የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መስራት

አለማጨስ

መጠጥ መቀነስ

ጤናማ ክብደት እንዲኖር ማድረግ

ጭንቀትን ማስወገድ

ቤት ውስጥ ግፊትን መለካት

ጠለቅ ያለ ወይም ረጅም አተነፋፈስ ልምምድ ማድረግ

> የጊንጪ ህዝብ እንቅስቃሴ በዚህ አልበቃም ቀጥሏል።በድል ላይ ድል እያስመዘገቡ ከረሙት የጊነጪ ህዝብ በመጨረሻ በፊንፊኔ ዙሪያ ያለውን የመሬት ወረራ እናወግዛለን ማስተር ፕላኑን እንቀወማለን ሲሉ ሰልፍ ወጡ። ይህ ተቃወሞ መላውን የኦሮሞ ህዝብ አንድ አደረገው።

የመንግስት ባለስልጠኑም ሰራተኛውም . . . ከ ገጽ 3 ዞሯል

አካል የለም በማለት ተማጽነው ቃል በመግባት ሠልፉ እንዲበተን ያደርጋሉ። ሰውም በሰላም ወደቤቱ ይመለሳል። ከሁለት ሶስት ቀን በከተማው የሚወራው ወሬ ይህ ብቻ ሆነ። በህፃናት ልጆቻቸው አነሳሽነት ያገኙት አሸናፊነት ስሜት ደስታን ፈጠረ። ህዝቡ አንድ እንዲሆንና እንድተማመን በር ከፈተ።

ከዚህ በፊት የከተማው ህዝብ ላለፈው 15 እና 20 ቀናት ሲያዝንበት የከረመበት አንድ የጋራ ጉዳይ አለ፡፡ እሱም የጭልሞ ጫካ ዛፍ ቀረጣ ጉዳይ ነው። ጭልሞ ጫካን ለማታውቁ ትንሽ ላሰተዋውቃችሁ። ጊንጪ ከተማ የምትገኘው ከአዲስ አበባ ወደ አምቦ ሲኬድ ከአዲስ አበባ ከተማ ፹፱ (89) ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ አነስተኛ ከተማ ነች። ከጊንጪ ከተማ ተነስተን ወደ አምቦ ከተማ በግምት 500 ሜትር እንደተጓዝን ደግሞ ወደ ቀኝ ታጥፎ የሚሄድ ኮሮኮንች (ፒስታ) መንገድ ይገኛል። ይህ መንገድ ወደ ጀልዱ ከተማና ግንደበረት ወረዳ የሚያደርስ ነው።በዚህ መንገድ ከጊንጪ ከተማ ተነሰቶ በግምት አንድ ኪሎ ሜትር እንደተጓዙ ጭልሞ ጫካን ያገኛሉ። ወደ ግንደበረት የሚጓዙ ከሆነ ጭልሞን መሐል ለመሐል አቋርጠው ይሄዳሉ። የጭልሞን ደን አቋርጠው ለማለፍ አሁንም በግምት ከ5-7 ኪሎ ሜትር መጓዝ የግድ ነው። ወደ ግራ እና ቀኝ ያለውም ስፋት ተመሳሳይ ነው። ይህ ጫካ ለአገራችንም ለአካባቢው ማህበረሰብም ትልቅ ባለውለታ ነው። በጣሊያን ወረራ ወቅት አርበኞች ጣሊያንን ሲዋጉ የነበሩት በዚህ ጫካ ተጠልለው ነው። በተለይ በሻለቃ ጃገማ ኬሎ (በመጨረሻም ሌ/ጀነራል) ይመራ የነበረው አርበኛ ቡድን ከፍተኛ ገድል ይፈጽም የነበረው በጭልሞ ጫካ ተገንነት ነው። በመሆኑም የአካባቢው ማህበረሰብ ለጭልሞ ጫከ ትልቅ ክብር አለው።

ሌላው ጭልሞ ጫካ ባለበት ረሃብና ስራ አጥነት የለም፡፡ ከጭልሞ ጫካ እርጥበ እንጨት መቁረጥ ክልክልም ነው።ነውርም ነው። የተወገዘ ነገር ነው። ለዚህ ነው ለዘመናት ተጠብቆ የኖረው። ነገር ግን ማንኛውም ሰው ጭልሞ ሄዶ ደረቅ እንጨት ለቅሞ ለቤቱ መጠቀም ወይም ሸጦ ለሚፈልገው ጉዳይ መጠቀም መብት ነው፡፡ ለዚህ ነው ጊንጪ ተቀምጦ ስራ አጣሁ፣ ተቸገርኩ ብሎ መለመን ነውር የሚባለው።ያጣ የቸገረው ሴትም ሆነች ወንድ ወደ ጭልሞ መሄድ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለፈው 15 እና 20 ቀን አካባቢ በጭልሞ አንድ ነገር ተከስቶ ህዝቡ ከአቅሙ በላይ ሀኖበት አዝኖ ተቀምጧል። ጉዳዩም ለሥርዓቱ ቅርብና እና በወቅቱ አባባል አንደኛ ዜጋ የሚባል አንድ ግለሰብ ጭልሞ ጫካን ገዝቻለሁ ብሎ ዛፉን እያስቆረጠ ደኑን እያስጨፈጨፈ በቀን እስከ 50 መኪና ሲጭን መታየቱ ነው። የአካባቢው ሽማግሌዎች ታዋቂ ሰዎች እንዴት ጭልሞ ይጨፈጨፋል ብለው ቢጠይቁ ከፌደራል ተፈቅዶ ነው ምንም ማድረግ አንችልም የሚል መልስ ይሰጣቸዋል።በዚህ ጉዳይ የኦሮሚያ ክልላዊ መነግስትም ዝምታን መርጧል።ህዝቡም እጅግ አዝኖ ከርሟል።ኳስ ሜዳውን በተቃውሞ ያስቀረው የጊንጪ ህዝብ ለምን የጭልሞን ደን ጨፍጭፎ አናስቆምም ብሎ ይነጋገራል፡፡ሁሉም በአንድ ድምጥ ይስማማል።በየአቅጠጫው ለገጠሩ ነዋሪም መልዕክት ይላካል።ጭልሞ በባለጊዜዎች

> እኛም ከአቅም በላይ ሆኖብን እንጂ እንዲጨፈጨፍ አንፈልግም ሲል የወረዳ አስተዳደሩ ሐሳቡን አጠናከረ። የከተማውም የገጠሩም ህዝብ በበአንድ ላይ ሆ ብሎ ወደ ደኑ ሲጠጋ ሲጨፈጭፋ የነበሩ ሰራተኞች እገር አውጭኝ ብለው ያመልጣሉ።ጭልሞም በዚህ ሁኔታ ተረፈ። ሆኖም ግን ቀላል የማይባል ጉዳት ደርሶበታል። የኢሰመጉ መርማሪዎች በአጋጣሚ በስፍራው ሄደን መታዘብ ችለናል።

እየተጨፈጨፈ ነው።ነገ ጥዋት በ12 ሰዓት ለተቃውሞ ሠልፍ እንድትወጣ የሚል መልዕክት ተላከ።በጊንጪ ከተማ ዙሪያ ያለው የደንዲ ወረዳ ህዝብ በአንድ ቀን ጥሪ ከተማውን አጥለቀለቀው።ሆ ብሎ ወጥቶ ቁጣውን ይገልፃል።ወደ ደኑ ሄዶ ባለሀብቱ ያሰማራውን ሠራተኞች ከደኑ ውስጥ አባረረ።የተቆረጠውም እንዳይጫን አገደ።ከዛሬ ጀምሮ አንድ መኪና ወደ ደኑ እንዳይገባ ለወረዳውን አስተዳደሩ ተናገረ። እኛም ከአቅም በላይ ሆኖብን እንጂ እንዲጨፈጨፍ አንፈልግም ሲል የወረዳ አስተዳደሩ ሐሳቡን አጠናከረ። የከተማውም የገጠሩም ህዝብ በበአንድ ላይ ሆ ብሎ ወደ ደኑ ሲጠጋ ሲጨፈጭፋ የነበሩ ሰራተኞች እገር አውጭኝ ብለው ያመልጣሉ። ጭልሞም በዚህ ሁኔታ ተረፈ። ሆኖም ግን ቀላል የማይባል ጉዳት ደርሶበታል። የኢሰመጉ መርማሪዎች በአጋጣሚ በስፍራው ሄደን መታዘብ ችለናል።

የጊንጪ ህዝብ እንቅስቃሴ በዚህ አልበቃም ቀጥሏል። በድል ላይ ድል እያስመዘገቡ ከረሙት የጊነጪ ህዝብ በመጨረሻ በፊንፊኔ ዙሪያ ያለውን የመሬት ወረራ እናወግዛለን ማስተር ፕላኑን እንቀወማለን ሲሉ ሰልፍ ወጡ። ይህ ተቃወሞ መላውን የኦሮሞ ህዝብ አንድ አደረገው።ማስተር ፕላኑን እንቀወማለን የሚለው እንቀስቃሴ በመላው ኦሮሚያ ከተሞች መደረግ ተጀመረ፡፡ቄሮ ተደራጀ።ሥርአቱን ቆርጦ መታገል ጀመረ።መፈክሩ ማስተር ፕላኑን አንቃወማለን ከሚለው አልፎ "ዳውን ዳውን ወያኔ" ወደሚለው መፈክር አደገ።ዓባይ ፀሐዬም ልክ እናስገባቸዋለን ሲል ፎከረ።ወያኔ/ኢህአዴግም ርህራሄ በሌለው መንገድ ጭፍጨፋን ቀጠለ።በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው የኢሰመጉ መርማሪዎች ጊንጪ ከተማ ገብተን የተፈፀመውን የመብት ጥሰት ለመርመራ የጀመርነው።የተፈጸመው የመብት ጥሰት በስፋትና በዝርዝር ተሰርቶ በኢሰመጉ መግለጫ የወጣ ስለሆነ ልለፈው።ጊንጪ ከተማ ውስጥ በዚያ አስቸጋሪ ሁኔታ ምርመራችን እንዳጠናቀቅን ጉዟችንን ወደ ግንደበረት አቡናስ ከተማና አካባቢው ቀጥሎም ወደ ጫልቺስ ከተማ ቀጠልን። በሚቀጥለው እትማችን በግንደበረት የታዘብኩትን አካፍላችኋለሁ።በቸር ሰንብቱ።

.... ይቀጥላል

> በግጭቱ ውስጥ ካሉ ኃይሎች መካከል አንዱ የጄኔቫ ስምምነቶች አካል ባይሆንም፣የስምምነቱ አካል የሆኑት ኃይሎች በጋራ ግንኙነታቸው ውስጥ እንደታሰሩ ይቆያሉ። የጄኔቫ ስምምነቶች በተጨማሪም ዓለም አቀፍ ያልሆኑ የትጥቅ ግጭቶች በልማዳዊ ዓለም አቀፍ ህጎች የሚገዙ ናቸው። በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች ያልተሸፈኑ ሁኔታዎች የሰው ስብዕና በሰብዐዊ መርሆዎች እና በሕዝብ ሕሊና ውሳኔዎች ጥበቃ ስር ሆነው የሚቆዩ መሆኑ ይታወሳል ።

ማይካድራ የዘመናችን . . .

ከ ገጽ 6 ዞሯል

በኩል በሚሰጡ ተደጋጋሚ መግለጫዎች እና እርምጃዎች የቀጠለው አለመስማማት፤ በመጨረሻም ጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም ከቀድሞው የትግራይ ክልል አስተዳደር በኩል በሰሜን ዕዝ ላይ ያደረሰውን ጥቃት ተከትሎ ወደ ትጥቅ ግጭት መቀየሩን ጠቅላይ ሚንስትሩ በይፋ መግለጫ ሰጡ።

የግጭቱ ምንነት

የግጭቱን ምንነት ለመወሰን በትጥቅ ግጭት ሁኔታ ውስጥ ተግባራዊ በሚሆነው የዓለም አቀፉ የሰብአዊነት ሕግ መነሻነት የምናየው ሲሆን ይህም ህግ በትጥቅ ግጭቶች ውስጥ የተሳተፉ ሰዎችን እና የሲቪል ሰዎችን ዕጣ ፈንታ የሚቆጣጠሩ ዓለም አቀፍ ሕጎችን ይይዛል፡ ፡ ይህ ህግ በሰብአዊነት ምክንያቶች የትጥቅ ግጭት ውጤቶችን ለመገደብ የሚሹ ህጎች ስብስብ ነው። በጦርነቱ ውስጥ የማይሳተፉ ወይም መሳተፍ ያቆሙ ሰዎችን ለመከላከል እና የጦርነት ዘዴዎችን እና መንገዶችን ለመገደብ ተግባራዊ ይደረጋል። ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ የጦርነት ህግ ወይም የትጥቅ ግጭት ህግ በመባልም ይታወቃል። በዚህ ህግ መሰረት ጦርነት ወይም የትጥቅ ግጭት አለ የሚባለው በሁለት ሉዓላዊ ግዛቶች መካከል የትጥቅ ግጭት ሲፈጠር ወይም በአንድ ሉዓላዊ መንግስት እና በተደራጁ ታጣቂ ቡድኖች መካከል ወይም በሁለት የተደራጁ ታጣቂ ቡድኖች መካከል መካከል የተራዘመ የትጥቅ ግጭት ሲኖር ነው። የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ሁለት አይነት የትጥቅ ግጭቶችን እውቅና ሰጥቷል እነሱም አለምአቀፍ የትጥቅ ግጭት እና አለም አቀፍ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት ናቸው።

እ.ኤ.አ. በነሐሴ 12 ቀን 1949 የተፈፀመው የጄኔቫ ስምምነቶች የጋራ አንቀፅ 2 ዓለም አቀፍ የትጥቅ ግጭትን ማለት በታወጀ ጦርነት ወይም በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የበላይ ተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊቀሰቀሱ በሚችሉ ሌሎች የትጥቅ ግጭት ሁኔታዎች ሙሉ፤ከሁለቱ በአንዱ እውቅና ባይሰጥም እንኳ፤ የሚደረግ ግጭት እንደሆነ ይገልጻል፡ ፡ በዚህ ምክንያት ግጭት እንደ ዓለም አቀፍ የትጥቅ ትግል ተደርጎ እንዲወሰድ የሚጋጩ ወገኖች ቢያንስ ሁለት ሉዓላዊ አገራት እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም በተጨማሪ ፕሮቶኮል 1 አንቀጽ 1 (4) ሰዎች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብታቸውን ለማስከበር እንደ የቅኝ አገዛዝ የበላይነትን ፣ የባዕዳንን የጦር ወረራ እና ዘረኛ አገዛዞችን (apartheid) የሚታገሉባቸውን ግጭቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ የታጠቁ ግጭቶች አካል እንደሆኑ ይደነግጋል። እንደነዚህ ያሉት ግጭቶች እንደ ብሔራዊ ነፃ የመውጣት እንቅስቃሴ ጦርነቶች ተደርገው የሚወሰዱ ሲሆን በዓለም አቀፍ የትጥቅ ግጭት ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ሁሉም የሕግ ጥበቃዎች በአንድ ግዛት ክልል ውስጥ ተወስነው ቢከሰቱም እንኳን ለእነሱም ተፈጻሚ ይሆናሉ። እንዲሁም ዓለም አቀፍ ያልሆኑ የትጥቅ ግጭቶችን አስቀድሞ የጦርነቱ አካል ያልነበረ ሉዐላዊ ሀገር የታጠቁ ተቃዋሚ ቡድኖችን ደግፎ ወደ ግጭቱ ከተቀላቀለ ዓለም አቀፍ ያልሆኑ የትጥቅ ግጭቶች ወደ ዓለም አቀፍ የትጥቅ ግጭትነት እንደሚቀየሩ የዓለም አቀፍ ፍ/ቤቶች ውሳኔ ያሳያል።

በሌላ በኩል ዓለም አቀፍ ያልሆነ የትጥቅ ግጭት የምንለው በጄኔቫ ስምምነቶች የጋራ አንቀጽ 3 መሠረት በአንድ በተወሰነ ክልል ውስጥ በመንግሥት እና በታጠቁ ተቃዋሚ ቡድኖች ወይም በሁለት ተቃዋሚ ኃይሎች መካከል የሚደረግ ግጭት ነው። በተጨማሪም አለም ዐቀፍ ያልሆኑ የትጥቅ ግጭቶችን ሰለባዎችን ለመጠበቅ በተደነገገው ተጨማሪ ፕሮቶኮል II አንቀጽ 1 በጥበቃው ስር ብቁ ለመሆን ተጨማሪ መስፈርቶችን ያስቀምጣል ይህም ከመንግስት ጋር የሚዋጋ ተቃዋሚ ቡድን ዘላቂ እና የተቀናጀ ሥራን ለማከናወን የሚያስችለውን የክልሉን የተወሰነ ክፍል መቆጣጠር፣ ወታደራዊ ክዋኔዎች እና ይህንን ፕሮቶኮል ለመተግበር በሚያስችል መልኩ በኃላፊነት ትእዛዝ ስር መሆን እንዲሁም እንደዚህ ያለውን ቁጥጥር በመፈፀሙ ተጠያቂ በሚሆን አዛዥ የሚመራ መሆን እንዳለበት ይገልጻል።

ምንም እንኳን በግጭቱ ውስጥ ካሉ ኃይሎች መካከል አንዱ የጄኔቫ ስምምነቶች አካል ባይሆንም፣የስምምነቱ አካል የሆኑት ኃይሎች በጋራ ግንኙነታቸው ውስጥ እንደታሰሩ ይቆያሉ። የጄኔቫ ስምምነቶች በተጨማሪም ዓለም አቀፍ ያልሆኑ የትጥቅ ግጭቶች በልማዳዊ ዓለም አቀፍ ህጎች የሚገዙ ናቸው። በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች ያልተሸፈኑ ሁኔታዎች የሰው ስብዕና በሰብዐዊ መርሆዎች እና በሕዝብ ሕሊና ውሳኔዎች ጥበቃ ስር ሆነው የሚቆዩ መሆኑ ይታወሳል ።

እ.ኤ.አ. የ1949 የጄኔቫ ስምምነቶች በሁሉም የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገራት የፀደቁ ሲሆን ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች እና ሌሎች የአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ ስምምነቶች ግን ተመሳሳይ ተቀባይነት ያለው ደረጃ ላይ አልደረሱም። ነገር ግን፣ በእነዚህ ስምምነቶች ውስጥ የተካተቱት አብዛኛዎቹ ህጎች እንደ ልማዳዊ ህግ አካል ተደርገው ተወስደዋል፣ እና እንደዚሁም፣ መንግስታት ራሳቸው ስምምነቶቹን ቢያፀድቁም ባያፀድቁም በሁሉም ግዛቶች እና በግጭቱ ውስጥ ያሉ ሌሎች አካላት ላይ ጭምር አስገዳጅ ናቸው። በተጨማሪም፣ ብዙ የልማዳዊ ዓለም አቀፍ ሕጎች በዓለም አቀፍም ሆነ ዓለም አቀፍ ባልሆኑ የትጥቅ ግጭቶች ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናሉ፣ በዚህ መንገድ ዓለም አቀፍ ባልሆኑ የትጥቅ ግጭቶች ውስጥ የሚሰጠውን ጥበቃ ማስፋት ተችሏል።

ኢትዮጵያም እ.ኤ.አ. የ1949 አራቱ የጄኔቫ ስምምነቶች እና የ1977 ተጨማሪ ፕሮቶኮሎቻቸው ፈራሚ ሀገር ናት። ነገር ግን ጥቅምት 24/2013 ዓ/ም ተጀምሮ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለው የትጥቅ ግጭት ምንም እንኳን በዋናነት የፌደራል መንግስቱን በሚወክለው በመንግስት የጦር ሀይሎች እና ለህወሃት ታማኝ በሆኑ ታጣቂ ሃይሎች መካከል የሚካሄድ ቢሆንም በተለያየ ጊዜ በግጭቱ ከተሳተፉትና እየተሳተፉ ካሉት አካላት ስብጥር እና ካላቸው ተሳትፎ አንጻር በዓለም አቀፉ የሰብአዊነት ሕግ ለትጥቅ ግጭቶች በሰጠው ትርጉም ወስጥ በአንዱ ብቻ ወስኖ ለማጠቃለል የማይቻል ሆኖ አግኝተነዋል።

የማይካድራ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ

ማይካድራ በመልክዐምድራዊ አቀማመጧ በምዕራብ ዞን ቃፍታ ሁመራ ወረዳ በጎንደር ሁመራ መንገድ ላይ የምትገኝ ሲሆን ከሂሞራ በስተደቡብ ከ30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ አብድራፊ በሚባል ከሚታወቀው ከምድረ ገነት ከተማ ደግሞ በሰሜን አቅጣጫ በ 60 ኪሎ ሜትር ርቀት የምትገኝ ለሱዳን ድንበርም በቅርብ ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ናት።

ይህች ከተማ በደርግ ዘመነ መንግስት በ1970ዎቹ ከጎንደርና ከወሎ በሰፈራ መልክ በሄዱ ሰዎች እንደተስፋፋችና እንደገና በኢህአዲግ ዘመነ መንግስት በ1980ዎቹ ከትግራይ ክልል በመጡ ሰፋሪዎችም ጭምር እንደሚኖሩባት ነዋሪዎቹ ይናገራሉ። የህዝብ ቁጥሩም ከ40000 እስከ 45000 የሚገመቱ የትግራይ፣የአማራ፣የወልቃይት እና የሌሎች ብሄሮች ተወላጆች ይይዛል። የአካባቢው ህዝብ አማርኛ እና ትግርኛ አቀላጥፎ የሚናገር ሲሆን በምእራብ በኩል የሱዳንን ጉርብትና አስታኮ አረብኛ ቋንቋንም የሚናገር ህዝብ ይሰተዋላል። የቋንቋ ስብጥሩና የህዝቡ ጥብቅ ትስስርን ከሚያንጸባርቁ ጉዳዮች መካከል በአካባቢው ያሉ ቦታ ስያሜዎች በሁለቱም ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ እና በትግርኛ የተሰየሙ ሆነው እናገኛቸዋለን።

በቋሚነት ከሚኖረው ህዝብ ባሻገር ዋነኝነት ከአማራ ክልል እንዲሁም ከሌሎች አካባቢዎች የተውጣጡ ሰላማዊ ዜጎች ለወቅታዊ ስራ ከከተማዋ ወጣ ብሎ በአካባቢው ነዋሪዎች “የበርሀ ሜዳ” እየተባለ በሚጠራው አካባቢ በሚገኙ ትላልቅ የሰሊጥ እና የማሽላ እርሻዎች ላይ ለመሰማራት ይሄዳሉ። እነዚህ የጉልበት ሰራተኞች በልማድ <<ሳሉግ>> በመባል የሚጠሩ ሲሆን በተለምዶ <<የጡት እናት/አባት>> በመባል በሚጠሩ ቤቶች ውስጥ በአንድ የጡት እናት ቤትም ከ5-10 የሚደርሱ የቀን ሰራተኞች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ሰራተኞች ለመኸር ስራ ከመስከረም ጀምሮ በዚያ ይገኛሉ። በጥቃቱ ሰለባ የሆኑት በአብዛኛው እነዚሁ በቀን ሥራ ላይ ተሠማርተው የሚኖሩ ሰላማዊ ሰዎች ናቸው።

የምርመራ ሥራው ዋና ዋና ግኝቶች

ጥቅምት 24/2013 ዓ/ም የተጀመረውን የትጥቅ ግጭት ተከትሎ በርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ያስከተሉ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ቆይተዋል። በተለይም ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ/ም በማይካድራ፣ ሁመራ፣ አብደራፊ፣ አብርሃጅራ እና ዳንሻ ከተሞች እጅግ የከፉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል። ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር እና በሌሎች አካላትም እንዳይጣሱ የመከላከል እንዲሁም የመጠበቅ ሃላፊነት በሰላም ጊዜ ብቻ ሳይሆን በግጭት ወቅትም ተግባራዊ መደረግ ያለበት ግዴታ ሆኖ ሳለ መንግስት ይህን ግዴታውን በአግባቡ መወጣት ባለመቻሉ ሰላማዊ ዜጎች ላይ አሰቃቂ የሆኑ የመብት ጥሰቶች ተፈጽመዋል።

.... ይቀጥላል

ኢሰመጉን ይርዱ

ኢሰመጉን ይርዱ
የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)
በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ተመዝግቦ በህጋዊነት
በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ መንግስተዊ ያልሆነ ሰብአዊ
መብቶች ተሟጋች ድርጅት ነው፡፡
ኢሰመጉ ለትርፍ የልተቋቋመ ነፃና ገለልተኛ
የሆነ ሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው፡፡

ዓላማውም

- በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲጎለብት አስተዋጾ ለማድረግ
- በኢትዮጵያ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን የበኩሉን ለመወጣት
- ለሰብአዊ መብቶች መከበር የበኩለን አስተዋጾ ለማድረግ

ሞያዊ፣ ቁሳቁሳዊና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ከኢሰመጉ ጋር ይስሩ፡፡
ኢሰመጉ

ኢሰመጉን ይርዱ